**የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር**
**8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ**
**ቃለ ጉባኤ ቁጥር 8**

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ፡- ፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ ዋና መ/ቤት
ቀን፡- ጥቅምት 20, 2014 ዓ.ም.
ሠዓት፡- ከጠዋቱ 3:00 - 4:30 ሰዓት

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ የንግድ ህግ አንቀጽ 367 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE/523/21 በመስከረም 21 ቀን 2014/ September 21,2021 በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ እንዲሁም በስልክ ጥሪ ተደርጓል፡፡

3. የጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ፣ ድምጽ ቆጣሪዎች እና በጉባኤው የተገኙ ዳይሬክተሮች

3.1 የጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና ድምጽ ቆጣዎች

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 3 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃይለማርያም ባዲሾ | ድምፅ ቆጣሪ |
| 4 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የጉባኤው ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ ዳይሬክተሮች፣

| ተ/ቁ | የዳይሬክተሮች ስም | በዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ያለው ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | የቦርድ አባል | |
| 5 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ /ተወካይ ወ/ሮ አይናለም | የቦርድ አባል | |

## 3.3 በጉባኤው ያልተገኙ ዳይሬክተሮች፤

| ተ/ቁ | የዳይሬክተሮች ስም | በዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ያለው ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ፀሐይ ፀጋዬ መከተ | የቦርድ አባል |
| 2 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | የቦርድ አባል |

## 3.4 በጉባኤው የተገኘ ታዛቢ- የለም

## 4. ምልዓተ ጉባኤ፣

ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 16

ጠቅላላ የማህበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 30,324

በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 11 የያዙት አክስዮን ብዛት 22,662

በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 5 የያዙት አክስዮን ብዛት 7,662

ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 10,108(33.33%)

በዚሁ መሠረት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 6 (ስድስት) እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 402 መሠረት ከማኅበሩ ባለአክስዮኖች 74.73% የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በጉባዔው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሣኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝርና የያዙትን አክስዮን መጠን የያዘ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet) (ሠንጠረዥ-1) ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

በንግድ ህግ አንቀጽ 380 መሠረት በጉባኤው ላይ ለድምጽ ቆጣሪነት ከባላአክሲዮኖች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሁለት አባላት ድምጽ ቆጣሪ ሆነው እንዲመረጡ ተጠይቆ፤ከተገኙት ባለአክሲዮኖች በአብዛኛው እኩል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ጉባዔው ከተገኙት ባለአክሲዮኖች ውስጥ ሁለት ባለአክሲዮኖች ድምጽ ቆጣሪ ሆነው እንዲመረጡ ያደረገ ሲሆን እነዚህም 1ኛ. አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚና 2ኛ. ወ/ሮ አለምነሽ ኃይለማርያም ባዲሾ ናቸዉ፡፡

## 5.የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፤

5.2. የተቋሙን የዋና መ/ቤት አድራሻ መለወጥን ስለማጽደቅ

5.3. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

6.1 አጀንዳ 5.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ

6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው ሊነጋገርባቸው ይገባል በማለት የቀረቡትን አጀንዳ በዝርዝር በማስረዳት ሊጨመር ወይም ከአጀንዳ ሊወጣ የሚገባ ካለ በማለት ጉባኤውን በመጠየቅ ፤ከጉባኤው የሚጨመር አጀንዳ ባለመኖሩ ለውሳኔ አቅርበዋል፡፡

6.1.2 ውሣኔ፣

ጉባኤው የቀረበው አጀንዳ በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

6.2 አጀንዳ 5.2. የማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ መለወጥን ማጽደቅ

6.2.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተዘራ ከበደ የአድራሻ ለውጥ የተደረገበትን ምክንያት ለጉባኤው አብራርተዋል፡፡ የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 372 የተመዘገበውን ህንጻ ወለል 4 እና 6 ተከራይቶ ይሰራ የነበረ ሲሆን ነገር ግን ማህበሩ የራሱ የሆነ ህንጻ ያስፈልገዋል በሚል የተቋሙ ማኔጅመንት ከአስተዳዳሪዎች ጋር በመነጋገር ለማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ህንጻ ግዢ ለመፈጸም ብዙ አማራጮችን በመፈለግ በመጨረሻም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 198 የሆነውን ባለ ሁለት ወለል ህንጻ ግዢ ፈጽሟል፡፡ በመሆኑም ማህበሩ የራሱ ህንጻ የገዛ በመሆኑ ዋና መሥሪያ ቤቱን ቀድሞ ተከራይቶ ይሰራበት ከነበረው ልደታ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 10፣ የቤት ቁጥር 372 ወደ ገዛው ህንጻ ወደሚገኝበት ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 198 መዘዋወር እንደሚገባ ተወያይቶበታል፡፡

6.2.2 ውሣኔ

የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ በ6ኛ አስቸኳይ ጉባኤ ላይ የተጠቀሰው ልደታ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 10፣ የቤት ቁጥር 372 ተቀይሮ ወደ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 198 ልዩ አድራሻ መስቀል ፍላወር፣ ከመስቀል ፍላወር ሆቴል ጀርባ እንዲዛወር ጉባዔው በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

7. ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች፣

ማህበሩ በሀምሌ 01 ቀን 2014ዓ.ም የፈጸመው የቤት ግዢ ውል

8. የጉባኤ ፀሀፊ ማረጋገጫ

እኔ የ<u>ፒስ ማይክሮፋይናንስ</u> አክሲዮን ማህበር የጉባኤው ፀሀፊ ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣ የፈረመዋቸው እና የከፈሉዋቸው አክሲዮኖች ብዛት በየስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በጥቅምት 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን

ማህበሩ 8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውንና በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፀን ውሣኔ ማሳለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማ አረጋግጫለሁ፡፡

| ተ/ቁ | የጉባኤ ፀሀፊ ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የጉባኤው ፀሐፊ | |

## 9. የዳይሬክተሮች ማረጋገጫ

እኛ የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ዳይሬክተሮች ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የመጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በጥቅምት 20 ቀን 2014ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 8ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔ ማሣለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለፁት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሣኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ/ቁ | የዳይሬክተሮች ስም | በዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ያላቸው ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | የቦርድ ሊቀመንበር | |
| 2 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | የቦርድ አባል | |
| 5 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ /ተወካይ ወ/ሮ አይናለም | የቦርድ አባል | |

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/10 ጽ/ቤት አ/አ
ፊርማው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል
ቁጥር ቆ10/00007492/ፊሰ/14
03/11/14

Documents Authentication & Registration Service Branch 10 Office

የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ አገልግሎት
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)
የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለበት ምክንያት
የገንዘብ ልክ ብር 416
በፊደል
ወይም ብር
የደረሰኝ ቁጥር 3119 የሆነ ቴምብር ተከፍሏል ።
3538 ቀን 20 14 ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ ሰብሳቢ አስፈፃሚ
ስም
ፊርማ